# ኢትዮጵያዊ ቁልፎች

ከዘፀአት በፊት በሚለው ጽሁፌ ላይ ወደ ሃገራችን መመለስ አለብን ነገር ግን ከዛ በፊት መንፈሳዊ ዝግጅት ያስፈልገናል ብዬ ነበር፤ ለዚህም አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦችን በዚች አጭር ጽሁፌ አቅርቤአለሁ። ርዕሱን ኢትዮጵያዊ ቁልፎች ያልኩበት ምክንያት በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሱት ቀላል ነገር ግን መሠረታዊ ነጥቦች እንደ እኔ ግምት ለችግራችን እንደ መክፈቻ ቁልፍ ናቸው ብዬ ፅኑ እምነት ስላደረብኝ ነው። አንብበናቸው የሚጠቅሙ ናቸው ያልናቸውን ልንጠቀምባቸው ግድ ነው፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በቻለው ሁሉ አስተዋጽኦ ያድርግ እየተባለ ነው፤ እኔም በአቅሜ እነሆ ይጠቅማሉ ያልኳቸውን ነጥቦች ታነቡልኝ ዘንድ በፍቅር እጠይቃለሁ።

## ነጥብ ፩

ለአንድ ቤት ጠንካራ መሠረት ያስፈልገዋል፤ በጠንካራ መሠረት የተገነባ ቤት ለብዙ ዘመን ያለምንም ችግር ይቆያል። ለእናት ኢትዮጵያና ልጆቿም እንደ ሃገር የመቆያ ዋናው መሠረታቸው ፍቅርና አንድነት ናቸው። ፍቅር ያስፈልገናል አንድነታችን የሚረጋገጠው ስንፋቀር ብቻ ነው። ብዙ ጠላቶች አሉብን ዋናው ስራቸው ደግሞ ይህንን መሠረታችንን ማበላሸት ነው፤ መሠረቱ ሲበላሽ እናት ኢትዮጵያ እንደማትኖር ያውቁታል እናም እየተሳካላቸው ይመስላሉ።
*ዘፋኙ አለ "እኛ ስንዋደድ ይሰማናል ጌታ"!!!*

## ነጥብ ፪

የበደለ አጥፍቷል፤ ይቅርታ ሊጠይቅ ግድ ነው። የተበደለው ግን ብድሬን እመልሳለሁ ብሎ ወደ በቀል ከገባ ያው የለመድነው አዙሪት ውስጥ ነው የምንገባው። ይቅር ማለትን መማር አለብን፤ እንደ እኔ ግምት እንደ ማንዴላ የተበደለ ሰው የለም ነገር ግን ልቡ ለይቅርታ ሰፊ ነበር፤ እናም ውጤቱ አስተማማኝ ሆነ። ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ፤ ፈሪ ሰው ሁልጊዜ ኃይልና በቀል ያበዛል፤ ልበ ሙሉ ደፋር ግን በራሱ እና በአምላኩ ስለሚተማመን ጊዜውን በበቀል አያጠፋም።
*ኢትዮጵያ እርቀ ሰላም ያስፈልጋታል።!!!*

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

**ነጥብ ፫**

ማንነትን መተው እና መናቅ የቅኝ ተገዢ ለመሆን መናፈቅ ነው። የቀድሞው ቅኝ ግዛት በኃይል ስለነበር አባቶቻችን በፈጣሪ እርዳታ ባደረጉት የአርበኝነት ተጋድሎ አዳኑን። ያሁኑ ግን ጠንካራ ነው፤ ይኸውም ጭንቅላትህን በመቀየር የሚከናወን ስለሆነ ነው፤ ብታምኑም ባታምኑም በጭንቅላት እንደተበለጥን እየታየ ነው። ለእኔ ብቁ ምሁር የምለው የራሱን ለሌሎች የሚያሳውቀውን እንጂ እነሱን ለመሆን የሚሮጠው አይደለም፤ ባለቤት ያቀለለውን..... ይላሉ አበው ሲተርቱ። እራሳችንን እና ማንነታችንን ልናከብርና ልናስከብር ያስፈልጋል፤ ማንነታችን የእኛነታችን ማህተም ነውና።
*ወደ ቀድሞ ነገር እንመለስ!!!*

**ነጥብ ፬**

እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው ማለት ሁሉም ሰው ከተጠቀመበት ከፍተኛ የአእምሮ ብቃት ተሰጥቶታል ማለት ነው። ፈረንጆቹ የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ቀላል ነው፤ እርሱም በተሰጠን ጭንቅላት ማመን ስንጀምር እድገቱና ውጤታማነቱ ይገኛል። እንዴ! እኛ ሁልጊዜ ተቀባይ መሆን ብቻ የለብንም፤ የኛንም ማሳየትና ማስፋፋት አለብን። አባቶቻችን ለዚህ ዓለም ድንቅ ነገሮችን ጥለው አለፉ እኛ ግን አንድ የዓባይን ውሃ እንኳ ገድቦ መጠቀም አቅቶን ስንዘፍንለት እንኖራለን። ከተጠቀምንበት የራሳችን ብዙ ጥበብና እውቀት አለን፤ ነገር ግን በመጀመሪያ ይሄ ብቃት እንዳለን በብርቱ ልናምን ይገባናል።
*ለሚያምን ሁሉ ይቻላል!!!*

**ነጥብ ፭**

ባለ ራዕይና እራሱን የሚያከብር ትውልድ መሆን ያስፈልገናል፤ አሁንማ እራሳችንን በራሳችን እየሰደብን እንገኛለን። ሃበሻ ምቀኛ ነው፣ ወረኛ ነው፣ ሃበሻ እንዲህ ነው.... እንዲያ ነው..... እያልን በሪሳችን እያላገጥን ነው። ከዛሬ ጀምሮ አንድ ነገር እንጀምር፤ ምቀኛ እንዳንባል ጥሩ ለሚሰሩና ላደረጉ ሰዎች ድጋፋችንን እንስጣቸው አብረናቸውም እንሰለፍ፤ ወገናቸውን የሚበድሉትን

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

የሚያዋርዱትን የሚጨቁኑትን እንገስፃቸው ከዚያም አልፎ በመጥፎ ሥራቸውም አንተባበር። እንዴ!! ወገኔ ምን ነካህ? ለውጥ እኮ የሚመጣው መጀመሪያ አንተ ስትለወጥ ነው። የራስህን ጉድፍ ሳታወጣ የሌላው እንዴት ይታይሃል? እራስህን ለማስተካከል ደፋ ቀና በል።
*የጭንቅላት ተኃድሶ ያስፈልገናል!!!*

<u>ነጥብ ፮</u>

ዘረኝነት፣ ጎሰኝነት እጅግ የተጠላ ነገር እንደሆነ አታውቅም? ከዘረኝነት በላይ የተዋረደና የድንቁርና እና የኋላ ቀርነት መገለጫ የለም። ወገኔ ኸረ ለመሆኑ አንተ ስትወለድ ፈጣሪህን አማክረህ ነው እንዴ ወደዚህ ምድር የመጣኸው? አንተ ፈልገህ ነው እንዴ ጎንደር የተወለድከው? ወይስ ወለጋ? ወይም መቀሌ? ወይም ወልቂጤ? ኸረ አስተውል! ዓለም ሲፈጠር አንድ አዳምና ሔዋን ተፈጠሩ በቃ ነጥቡ ይኼ ነው። ሰው በሰውነቱ እንጂ በተራራና በወንዝ እንዲሁም በመንደር ማመን ከጀመረ የውድቀት ጣራው ላይ ደርሷል ማለት ነው። በመከፋፈል እና በጎጠኝነት የምታመጣው አንዳች ለውጥ አይኖርም። የዘረኝነት ትርፉ ጥላቻ ብቻ ነው፤ጥላቻ ደግሞ የአእምሮ ውድቀት ነው።
*ከሣጥኑ ውጪ ልናስብ ግድ ነው!!!*

<u>ነጥብ ፯</u>

ሃገራችን እውነቱን ለመናገር እጅግ በጣም ሃብታም ምድር ነች። ብዙ ገና ምንም ያልተነካ የመሬት ውስጥ ሃብት አላት፤ ዋናው ቁም ነገር ይኽንን ነገር ለሕዝባችን ጥቅም እድገትና ብልጽግና እንዲሁም የደስታ ምንጭ ማዋሉ ላይ ነው። በውጭ ተበትነን ያለነው ወገኖች ጠቅላላ ፊታችንን ወደ ሃገራችን ማዞር አለብን፤ እናም ወገናችንን ባለን እውቀት እና ብርታት ማገልገል አለብን። ፈረንጆቹ አባቶቻችንን በሃይል ስላልቻሉ አሁን እኛን ልጆቻቸውን በእርዳታ እያሽመደመዱን ነው፤ በጀታችንን በእነርሱ እርዳታ ላይ አርገናል፤ እንዲሁም ከሕዝባችን አብዛኛው ያው አንድኛቸውን እነርሱ ይግዙን ማለት ጀምሯል። አይበለውና ትርምስ ቢፈጠር እናረጋጋ ብለው ይገቡና ሲያልሙት የቆዩት የዘመናት ቁጭት ከልብ ይደርሳል። ሃገራችንና ሕዝባችንን ከልመና ማውጣት አለብን።
*መፅሐፉም ብሷል "ከመለመን ሞት ይሻላል"!!!*

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

## <u>ነጥብ ፯</u>

ቀናውን መንፈስ በሕዝባችንና በወገናችን ላይ ማስረጽ መጀመር አለብን። ክፉም ሆነ ጥሩ ስሜት የመዛመት ባሕሪይ አለው፤ ስለዚህ ጥሩ ጥሩውን ስሜት ማዛመት መቻል አለብን። ሃገራችንን መለወጥ እንደሚቻል፣ ያለውን የክፋት መንፈስ ማስወገድ እንደሚያስፈልግ፣ የተፈጥሮ ሃብቱን አውጥተን መጠቀም እንደምንችል፣ ብቃት የሚፈጠረው ጠንክሮ ከመሥራት እንደሆነ ወዘተ አንዱ ለሌላው ማሳወቅ እና ማስታወስ ያስፈልጋል። ከምንም በላይ በተመረዘ እና በጥፋት ላይ ያለውን የአገር አመራር ቡድን እና የታወሩ ደጋፊዎቹን በቅዱሱ መንፈስ ከዚህ ካሉበት የክፋት አስተሳሰብ ነፃ ማውጣት አለብን፤ የነፃነት ትግሉ እኛን ሳይሆን እነሱን ነው አርነት የሚያወጣቸው። እናም እኛ ሰላሙንና ፍቅሩን በመሣሪያና በጦርነት ሳይሆን በፍቅርና በመግባባት መንፈስ ማምጣት አለብን፤ ፍቅር ሁሉን ያሸንፋል፤ በሃይል የሰውን ልብ መግለጥ አይቻልም፤ በፍቅር የታነፀ ግን እንኳን ሰውን አምላኩንም ያሸንፋል።
ጠላትህን እወቅ! ጠላትህ ክፉ መንፈስ፣ ምቀኝነት፣ ስግብግብነት፣ ውሸት፣ ፍቅር ማጣት፣ ኅሰኝነት፣ መነካከስ፣ ስንፍና፣ ጥበብ ማጣት፣ ጥል እና የመሳሰሉት ናቸው። ስንፍናን በእውቀት ታጠፋዋለህ፤ እውቀት ደግሞ ከጥበብ ነው፤ ጥበብ ደግሞ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ ፍቅር ነው።
*በሰይፍ የሚኖሩ በሰይፍ ይወድቃሉ!!!*

## <u>ነጥብ ፰</u>

ሃገር በአንድ ቀን አትገነባም፤ ነገር ግን ባለ ራዕይ እና ከቂም በቀል ውጪ የሆነ ትውልድ ሲነሳ ሣር ቅጠሉ ሳይቀር እልል ይላል፤ ልጆቿም ጠግበው ማደር ይጀምራሉ። አካሄዳችን ፈጣሪያችንን ደስ ካሰኘው ሰላሙን ያወርድልናል። መሪ ለሕዝቡ እንደ አባት ሊሆን ግድ ነው፤ አባት ደግሞ ከልጅ ልጅ አያዳላም፤ መምራት ያልቻለ ደግሞ አቅቶኛል አበላሽቻለሁ ይበቃኛል ማለት አለበት። ትልቅ አዋቂ የሚባለው መሪ ራሱን ዝቅ ማድረግ የሚችል መሪ ነው፤ ከራሱም ይልቅ ወገኑን ሊወድ ግድ ነው፤ትውልድ እኮ መሞከሪያ ሊሆን አይገባም። የሃይማኖቱ መሪ መድረኩ ላይ ወጥቶ የሚሰብከውን ትምህርት እራሱ በተግባር ማሳየት አለበት፤ እምነት በስራ ይገለፃል ስለዚህም ስለ መንፈስ ልጆቹ ሊዋደቅ ይገባዋል። መሪ መሆን ቀላል ነገር አይደለም ጥበብና ትዕግስት ማስተዋልም ይጠይቃል። አባት የቤተሰቡ መሪ ነው፤ ስለዚህም ብቁ እና ንፁህ ዜጋ

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

ለመፍጠር ልጆቹን በፍቅርና በቤተሰባዊ መተሳሰብ ማሳደግ አለበት፤ ልጆቻችን የእኛ ነፀብራቅ ናቸው። ልጅህ ፊት ስለ ጎሳ፣ ስለ በቀል ወዘተ ስትናገር ነገ እርሱም በአደባባይ ያንኑ ነው የሚገልፀው። ለልጅህ መልካም ስብዕና አውርሰው ከዛ ሃገርህ ሰላም በከበበው ትውልድ ትሞላለች።
*አዋቂና ጥበበኛ ትውልድ ሲነሳ ሃገር ትቀናለች!!!*

<u>ነጥብ ፲</u>

እግዚአብሔር ሃገርን ካልጠበቀ ጠባቂዎች በከንቱ ይለፋሉ፤ በምንለፋበት እንዲሁም ደፋ ቀና በምንልበት ሁሉ ፈጣሪያችን አብሮን ካልወጣ ከንቱ ድካም ነው። ስራችንን ከላይ ሆኖ በበላይነት የሚመራው እርሱ ቸሩ ፈጣሪያችን ነው፤ ስራችንን እንዲያቀናልን እኛ ደግሞ እርሱ በሚሳተፍበት ማዕቀፍ ውስጥ መሆናችንን ማረጋገጥ አለብን። በምቀኝነት፣ በጎሰኝነት፣ በመወነጃጀል፣ በጥል፣ በክርክር፣ በፍቅር ማጣት፣ በስንፍና እና በመሳሰሉት ውስጥ ሆነን አምላካችን እንዲረዳን መጠበቅ የለብንም። የእኛ ዋናው ሥራ ከልብ መዋደድ ነው፤ ይኼኔ አምላካችን ክብሩን ይገልፃል። ደም መፋሰስ በሃገራችን የሚቆመው ሁሉም ሰው ጦሩና ሰይፉን ወደ ማረሻ መሣሪያ ሲለውጠው ነው፤ ከሃያላኑ ሃገር በመሣሪያ ብቻ ብዙ እዳ አለብን፤ ስለዚህ አሁን ወደ አእምሮአችን የመመለሻው ጊዜ ነው። የለመድነው ዑደት ውስጥ ተመልሰን እንዳንገባ ይኸንን አፍዝ አደንግዝ አሽቀንጥረን መጣል አለብን።
*በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፤ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል!!!*

<u>ማጠቃለያ</u>

ሃገራችን ሰፊ ናት ለሁሉም ትበቃለች፤ ስለዚህ ወደ ሃገራችን መመለስና ማቅናት አለብን። በስደት ያለነው ወገኖች ሁሉ ምንም ጊዜ ሳንሰጥ ብሔራዊ እርቁንና መግባባቱን ልንጀምር ግድ ነው፤ ከዚያ ሳናስበው ይኼ ነገር ሃገር ቤትም ደርሶ እናየዋለን፤ የምንፈልገው ለውጥም ይመጣል። ልንከባበር ያስፈልጋል፤ ማንም ታላቅ ታናሹን አይናቀው፤ ታናሹም ታላቁን ያክብር፤ መከባበር የእውቀት መገለጫው ነው። በነገራችን ላይ ዓለም አሁን በሁሉ መልኩ ጥሩ አይደለም፤ በተለይ የምግብና የውሃ እጥረት ብዙዎችን ሃገሮች አሳስቧል፤ ስለዚህም ብዙ ሃገሮች የሰውን ሃገር መሬት በገንዘብ እየወረሩ ነው። እኛ እዚህ ቁጭ ብለን የሃገራችን ለም መሬት የሌላ የባዕዳን ሕዝቦች የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ሲሆን

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

እያየን ነው። ወደ ምድራችን ተመልሰን ብንበረታ ከራሳችን አልፈን ለአህጉራችንም እንተረፋለን።

የኢትዮጵያ አቀማመጥ በመልክዐ ምድርም ሆነ በምጣኔ ሐብት ስትራቴጂክ ነው፤ በአቀማመጥ ከሳህራ በታች ያለውን ክፍል ከእሲያና አውሮፓ በገበያ ለማገናኘት ምቹ ቦታ ነው። በምጣኔ ሐብታዊ ረገድ እኔ እራሴ የማውቀው ከፍተኛ የነዳጅ ክምችት አለ (ለዚህ ማስረጃ ደግሞ የአሜሪካንን የነዳጅ ጥናት ውጤቶች ማንበብ ይቻላል)፤ እንደውም ስለዚህ ጉዳይ ከአንዳንድ ባለሙያዎች ጋር ስነጋገር ሳውዲ አረቢያ በድፍድፉ ውስጥ ያለውን ሰልፈር የተባለ ንጥረ ነገር ለማጣራት ብዙ ውጪ እንደምታወጣ ነገር ግን የእኛ መጠኑ አነስተኛ ስለሆነ የምርት ወጪያችንን እንደሚቀንስልንና ተመረጭነት እንዳለው አስረድተውኛል። እንደሚባለው በኦጋዴን ብቻ አይደለም የነዳጅ ክምችት ያለው፤ በጋምቤላ እንዲሁም አሁን ሸፍጠኛው አገዛዝ ለሱዳን በሰጠው የጎንደር ክፍል ከፍተኛ አስገራሚ ክምችት ይገኛል።

በሃገራችን ብዙ ወንዞች አሉ፤ እንዚህን ለግብርናና ለመጠጥ ለማዋል እውቀቱ ከእኛ ነው የሚጠበቀው። በሃገራችን ፀሐይ አመቱን ሙሉ አለ፤ እንዲሁም የድንጋይ ከሰል በብዙ ቦታዎች እንዳለ በማስረጃ አውቃለሁ፤ ስለዚህም ለኃይል አቅርቦታችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። እንደዚሁም ዩራኒየም የተባለውን ንጥረ ነገር ያገኘው ሰው ከነ ምስክር ወረቀቱ አሳይቶኛል፤ስለሆነም አንድ ቀን እንደ አደጉት ሃገሮች የኒውክሊየር ሃይልን ልንጠቀም እንችላለን ማለት ነው። በማዕድን ሃብቶች ብዙ ነገር እንዳለን እንደውም ከእኔ በላይ የሚያውቁ ብዙ የሃገራችን ምሁራን በውጭ ሃገር ይገኛሉ።

አሁን በሃገራችን በአመራር ያለው የክፉት ቡድን ዘረፈ የሚባለውን ገንዘብ በቅጡ ባላውቀውም እንደ እኔ ግምት ግን ከምንም አልቆጥረውም ለምን ቢባል ለውጥ ሲፈጠር በእኩልነት እንሳተፍ ቢባል መዝረፍ የለመደ ጭንቅላት አእምሮውን እና ትጋቱን ተጠቅሞ ከሚሰራው ጋር ሊውዳደር ቀርቶ የጨዋታው ሜዳ እንኳን አይገባውም። በጥረት ማምጣት እና በማጭበርበር ማግኘት ሊወዳደሩ አይችሉም፤ ስለዚህም እነሱ ስለዘረፉት ገንዘብ እያወራን የምናጠፋው ጊዜ የለንም።

የአንድ ሃገር ዜጋ ከመሆን ጋር ኃላፊነትም አብሮ ይመጣል፤ ሁላችንም ለሃገራችንና ለወገናችን ግዴታ አለብን። እኔ ለምሳሌ ወደ ሃገራችን ዘፀዐት

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

ካደረግን በኋላ እስከ አስር ቢሊዮን ለአገራችንን የሚያመጣ የልማት እንቅስቃሴ እጀምራለሁ፤ ለዚህ እውቀቱም ገንዘቡም ግንኙነቱም አለኝ።

ሃብቱ እንዳለን ሁሉም ያውቀዋል ነገር ግን እኛ ስናድግ የሚሰጉ የጠላት ሃገሮች ስላሉ እኛን ለማናከስ ቀን ከሌት ይለፋሉ ስለዚህ የመጀመሪያው ዓበይት ነገር መዋደድና መፋቀር ነው።

ሁሌም አባቶቻችንና እናቶቻችን ሲፀልዩ እንዲህ ይላሉ
"አምላካችን ሆይ ኢትዮጵያ ሃገራችንን እምነትን በማያስለውጥ አንድነትንና ፍቅርን በማያናውጥ መልኩ የስልጣኔን በር ክፈትላት" ይላሉ።
አዎ ፈጣሪ ከሁሉም በላይ የፍቅርን በር ይክፈትልን!

ቸሩ ፈጣሪያችን ሃገራችንና ሕዝባችንን ሁሉ ይባርክልን።
*እኛ ታላቅ ነን! ልባችንም!*

ከበትረ ሙሴ

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)